# የድነት (Salvation) ትምህርት

## 1. የሰው አፈጣጠርና ውድቀቱ፤

*ሰው ክቡርና ውድ ሆኖ ሳለ ኃጢአት ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ለየው።*
*ኃጢአት የሰውን ታሪክና መንፈሳዊ መልኩንም አበላሸበት!*

## 1.1 ሰው ክቡርና ውድ ፍጡር መሆኑ፤

መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ከፍጥረት ሁሉ መካከል የተለየ ክቡርና ውድ ፍጡር መሆኑን ይገልጻል። ዘፍ 1፥26–28 ያሳያል።

### 1.1.1 የፍጥረታት አመጣጥና ሰው በእግዚአብሄር አምሳል መፈጠሩ፤

ሀ) አፈጣጠሩ ከሌላው መለየቱ

1) ሰው በእግዚአብሄር መልክ እንደምሳሌውም ተፈጥሮአል፤
ዘፍጥ 1፥26–27፣ ያዕ 3፥9።

2) ከእግዚአብሔር እስትንፋስ አግኝቶአል፤
ዘፍጥ 2፥7፣ ኢዮብ 33፥4

3) ከሌሎች ፍጥረቶች በተለየ መንገድ ተፈጥሮአል፤
በትዕዛዝ ብቻ የተገኘ ሳይሆን በአምላኩ እጅ ተበጅቶአል፤ ዘፍ 2፥7፣ ኢዮብ 10፥8–10።

ለ) ከመለኮት ባህርይ ተካፋይ እንዲሆን የተሰጠው ነው፡፡
(ፍቅር፣ ምህረት፣ እውቀት፣ ራስን መግዛት፣ መጽናት፣ እግዚአብሔርን መምሰል።)
2ኛ ጴጥ 1፤ 2-4 ፣ ሮሜ 5፣5 ፤ 1ኛ ዮሐ 4፣11፤
1ኛ ቆሮ 1፣30፤ 2ኛ ጴጥ 1፤16

ሐ) ዘላለማዊነቱ፤ (ከሞት በኋላም የሚኖር መሆኑ)፤
ማቴ 25፥46፣ ሉቃ 16፣19-31፤ ዳን 12፣2

መ) የመሥራትና በማስተዋል ችሎታው፤
ዘፍጥ 2፥15 ኢዮብ 32፥8

ሠ) ለመግዛት ስልጣን የተሰጠው መሆኑ «ግዙአትም...»
ዘፍጥ 1፥28፤ መዝ 8፣6

**Can also be downloaded from:**

*http://www.j-e-c.org/faceliftup/Ministries/EvangelismMinistry/Salvation%20Teaching%20(Final_version).pdf*

## 1.1.2 ለሰው የተሰጠው ስልጣንና የተደረገለት እንክብካቤ

1) ምቾቱ እንዲጠበቅ የሚያስፈልገውን ነገር ተሟልቶ በተዘጋጀለት ገነት ውስጥ እንዲኖር መደረጉ፤ ዘፍጥ 2፥8–15።

2) በዓለም ከሚገኝ ፍጥረት ሁሉ በላይና ገዥ መደረጉ፤ ዘፍ 1፥28 መዝ 8፥5–9።

3) ማንም የማይወስድበት ነጻ ምርጫ የተሰጠው መሆኑ፣ ዘፍ 2፥16–17

ሰው ነጻ ምርጫ ያለው በመሆኑ አምላኩን እንዲያመልክ የተደረገው በመገደድ ሳይሆን በፈቃደኝነት ብቻ ነው።
ዘጸ 30፥19፣ መዝ 109፥17–19፣ ሉቃ 9፥23–25

ከዚህ ሁሉ የምንገነዘበው ሰው በእግዚአብሔር ፊት የተከበረና የተወደደመሆኑን ነው። መዝ 139፥13–18።

## 1፣2 የሰው ሁለንተና (መንፈስ፣ ነፍስ፣ ሥጋ)

መንፈስ፤

- ሰው ከእንስሳት የሚለየው የእግዚአብሄር እስትንፋስ የሆነ መንፈስ የተሰጠው በመሆኑ ነው (ዘፍ 2፣7)
- ሰው ከእግዚአብሄር ጋር ሕብረት የሚያደርገው በመንፈሱ አማካኝነት ነው (ዮሐ 4፣24 ፣ ሮሜ 8፣16)
- የመንፈሳዊው አለም ግንዛቤ የምናገኘው በመንፈሳችን ነው (1ኛ ቆሮ 2፣13)

ነፍስ፤

- ስሜት፣ ፈቃድና አእምሮ የያዘ የማንነታችን ማእከል ነው
- የራስ (የእኔ) ግንዛቤ የምናገኘው በነፍሳችን ነው

ሥጋ፤

- አምስቱ የስሜት ህዋሳት (ማሽተት፣ ማየት፣ መስማት፣ መዳሰስና መቅመስ) የያዘ የማንነታችን ማእከል
- በአካባቢያችን ያለው አለም ግንዛቤ የምናገኘው በሥጋችን ነው፡፡

**ለአስተማሪዎች፤**

- **ህሊና** «ልባችንስ በሚፈርድብን ነገር ከእውነት እንደሆንን በዚህ እናውቃለን»
- **ስሜት**፣ (ምኞት፣ ደስታ፣ ሃዘን፣ ጥላቻ ወ.ዘ.ተ. የሚካሄድበት ማእከል)
- **አእምሮ** (ሃሳቦቻችንን የያዘ የማንነታችን ማእከል ነው፣ ማመዛዘን፣ እንዲህ ቢሆን እ ንዲህ ነው የሚለው የማንነታችን ማእከል)
- **ፈቃድና** («ይሄንን አደርጋለሁ»፣ «ይሄንን አላደርግም»፣ «ይሄንን እወዳለሁ»፣«ይሄ ንን አልፈቅድም» የሚለው ማእከል

Can also be downloaded from:

http://www.j-e-c.org/faceliftup/Ministries/EvangelismMinistry/Salvation%20Teaching%20(Final_version).pdf

# 1፤3 የሰው በኃጢአት መውደቅ (መንፈሳዊ ሞት)

## ሀ) ኃጢአት ምንድነው?

1) **ኃጢአት ዓመጽ ወይም አለ መታዘዝ ነው።**

**አዳምና ሔዋን ለእግዚአብሔር አልታዘዙም።** 1ዮሐ 5፥17

2) **ኃጢአት የእግዚአብሔርን መንገድ ትቶ በራስ መንገድ መሄድ ነው።**

**ኢሳ** 53፥6

## ለ) ሰው በኃጢአት እንዴት ወደቀ?



ሰው ለዘላለም የሚኖር ነፍስ ሆነ ፤ ዘፍጥ- 2፡7 ። ሥጋው ሞቶ ወደ
ይመለሳል ። መንፈሱ ግን አይሞትም ። እንስሳ ለዘላለም የሚኖር
የለውም ።
3/ እግዚአብሔር ለሰው በምድር ላይ ያለውን ፍጥረት ሁሉ እንዲገዛ
ጣን ሰጠው ፤ ዘፍጥ- 1፡28 ።
4/ እንስሳ ከሰው የተለየ ፍጥረት ስለሆነ ለአዳም እንደ እርሱ ያለ
ከእንስሳት ወገን አልተገኘለትም ፤ ዘፍጥ- 2፡20 ። በዚህ ምክንያት
አብሔር ሔዋንን ፈጠረለት ።

እግዚአብሔር ለሰው የሚያስፈልገውን ሁሉ ሰጠው ፡-
1/ ምግብ ሰጠው ፤ ዘፍጥ- 1፡29 ።
መኖሪያ ሰጠው ፤ ዘፍጥ- 2፡15 ።
ረዳት ሰጠው ፤ ዘፍጥ- 2፡22 ።
ኃላፊነት ሰጠው ፤ ዘፍጥ- 1፡26-28 ።
2/ ለሰው ምርጫን ሰጠው ፤ ዘፍጥ- 2፡16-17 ። ሰው መታዘዝን ወይም
መታዘዝን ሊመርጥ ይችላል ። ሰው በግድ ሳይሆን በምርጫው
አምኖ በፈቃደኝነት እንዲታዘዝለት እግዚአብሔር ፈለገ ።

መ/ እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ለምንድነው ?
1/ ሰውን የፈጠረው ለራሱ ክብር ነው ፤ ኢሳ- 43፡7 ።
2/ ሰውን የፈጠረው እንዲያመልከውና እንዲያመሰግነው ነው ፤
102/103፡1-2 ፤ 106/107፡1 ፤ ፊልጵ- 2፡10-11 ።

ትምህርት 11

ጥያቄ 15 ፡- ኃጢአት ማለት ምን ማለት ነው ?
መልስ ፡- ኃጢአት ማለት ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ማለት ነው ፤ 1ዮሐ- 3፡4

ኃጢአት

ሀ/ ሰው በኃጢአት እንዴት እንደወደቀ ፤ ዘፍጥ- 3 ።
1/ ሔዋን የሰይጣንን ምክር ሰማች ። ሰይጣን የእግዚአብሔርን
ፍቅር እንድትጠራጠር አደረጋት ፤ ዘፍጥ- 3፡1፡4፡5 ።
2/ ሔዋን የሰይጣንን ምክር ስለሰማች የተከለከለው የዛፉ ፍሬ ቆንጆ
ሆኖ አየች ። በልብዋም ተመኘች ፤ ዘፍጥ- 3፡6 ። ሰይጣን ዛሬ ደግሞ
ሮአችን ፣ በዓይናችንና በልባችን ይፈትነናል ፤ 1ዮሐ- 2፡15-17 ።

24

3/ ፍሬውን ወስዳ በላች ። ለባልዋም ሰጠችው ። እርሱም በላ ፤ ዘፍጥ- 3፡፡
4/ ሰዎች ሁሉ የአዳም ልጆች በመሆናቸው ኃጢአተኞች ሆኑ ፤ ሮሜ 5፡12

ለ/ ኃጢአት ምንድነው ?
1/ ኃጢአት ዓመፅ ወይም አለመታዘዝ ነው ፤ 1ዮሐ- 5፡17 ። አዳምና
ለእግዚአብሔር አልታዘዙም ።
2/ ኃጢአት የእግዚአብሔርን መንገድ ትቶ በራስ መንገድ መሄድ
ኢሳ- 53፡6 ።
3/ ኃጢአት በጎ አለመሥራት ነው ፤ ያዕ- 4፡17 ።
4/ ሰው በሚናገረው ቃል ኃጢአት ሊሠራ ይችላል ፤ ማቴ- 5፡21-22 ፤
ያዕ- 3፡10 ።
5/ ኃጢአት ከሰው ልብና ምኞት ሊወጣ ይችላል ፤ ምሳ- 4፡23
6፡10 ።
6/ የኃጢአት ዓይነቶች በገላ- 5፡19-21 ተዘርዝረዋል ።

ትምህርት 12

ጥያቄ 16 ፡- የኃጢአት ደመወዝ ምንድነው ?
መልስ ፡- የኃጢአት ደመወዝ የዘላለም ሞት ነው ፤ ሮሜ 6፡23 ።
ጥያቄ 17 ፡- ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው ?
መልስ ፡- አዎን ፣ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው ፤ ሮሜ 3፡23 ።
ጥያቄ 18 ፡- ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን የሚያውቀው እንዴት ነው ?
መልስ ፡- ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን የሚያውቀው የእግዚአብሔር ቃል ሲያመ
ክተውና መንፈስ ቅዱስ ሲወቅሰው ነው ።

የኃጢአት ውጤቶች

ሀ/ ኃጢአት መሥራት በዚህ ዓለም ያስከተላቸው
1/ መከራና ድካም ፤ ዘፍጥ- 3፡19 ።
ዘፍጥ- 3፡16-18 ።
2/ ፍርሃትን አስከተለ ። ኃጢአትን ሳይሠሩ
አብሔር ጋር ይገናኙ ነበር ። ከሠሩ በኋላ ግን
ሊደበቁ ሞከሩ ፤ ዘፍጥ- 3፡8 ።
3/ በሽታንና ሞትን አመጣ ፤ 1ቆሮ- 11፡30-31 ፤ የሐዋ-

25

የፎቶውን ይዘት ይመልከቱ

## ሐ) ኃጢአት በሰው ላይ ያስከተላቸው ውጤቶች፤

1) **ፍርሃትን (ዘፍ 3፤8)/እፍረትን/ከእግዚአብሄር ሽሽትን አስከተለ**

2) **የተራቆተና ከእግዚአብሔር ፊት መቆም የማይችል አደረገው፤**
**ዘፍጥ** 3፥6–10፤ **ራዕይ** 16፥15፤ **ኢሳ** 6፥1–5፤ 64፥6–7።

3) **ጠላትነትን ፈጥሮበታል፥**
- **ከእግዚአብሔር ጋር በማጣላት ለይቶታል፤**
  **ዘፍ** 3፥8–11፤ **ኢሳ** 59፥1–8።
- **ሕይወቱን በመመረዝ ከራሱ የተጣላ አደረገው፤**
  **ዘፍ** 4፥6–7, 13–14፤ **ማቴ** 27፥3–7 ።

Can also be downloaded from:

http://www.j-e-c.org/faceliftup/Ministries/EvangelismMinistry/Salvation%20Teaching%20(Final_version).pdf

– ሰውን እርስ በርሱ እንዳይስማማ በማድረግ
ለያየ ው፤ ዘፍ 3፥11–13፤ 4፥3–8 2ዜና 15፥3–6።

4) የገነት ኑሮውንና የሥልጣን ደረጃውን እንዲያጣ አደረገው።

– ከገነት ተባረረ፤ ዘፍ 3፥22–24።

– ተፈጥሮ የሚያምጽበት ሆነ፤ ዘፍጥ 3፥17–18፣ 4፥12።

5) ከእግዚአብሔር እርግማን ውስጥ እንዲኖር አደረገው ለበሽታ፣ ለረሃ ብ፣ ለራቁትነት፣ ለቸነፈር፣ ለድካም፣ ለመከራ ሁሉ ወዘተ የተጋለጠ ሆነ። ዘፍ 3፥1፣ 6–19፤ ኤር 5፥23–25።

6) ለባርነት የተዳረገ ሆነ፤

– የሰይጣን ባርያ በመሆን ፈቃዱን ይፈጽማል፤
ሉቃስ 4፥5–6፤ 1ዮሐ 5፥19 ኤፌ 2፥2።

– የኃጢአት ባርያ በመሆን ለሥጋው ተገዥ ሆኖ ይኖራል፤
ዮሐ 8፥14–34፤ ቲቶ 3፥3፤ 2ጴጥ 2፥19።

7) ሞትን አስከትሎበታል፤

– መንፈሱን በማደንዘዝ ከእግዚአብሔር ለይቶ ሙት አደረገው።
ኤፌ 2፥1–3፤ 4፥18–19፤ ቆላስ 2፥13።

– በሥጋው ሞቶ የሚበሰብስ አደረገው፤
ዘፍ 3፥19፣ ሉቃ 12፥20፤ መክ 12፥7።

– ከእግዚአብሔር ለይቶ ለዘላለም በገሃነም እንዲኖር አደረገው
ይህም ሁለተኛው ሞት ነው። ሕዝ 18።4፣ 18–20፣
ማቴ 25፥44–46፣ ራዕይ 20፥11–15፤ 21፥8

በእግዚአብሔር የተወደደና ግሩምና ድንቅ የተባለው ሰው መዝ. (139)፥13–18)ቃል ኪዳን በማፍረሱና ለኃጢአት ኃይል ተገዥ በመሆኑ ማን ያድነኛል ብሎየሚጮህ (ሮሜ 4፥24) ተሸናፊ ፍጡር ሆኖ ይታያል።

## 1፤4 እግዚአብሄር ለሰው የገባው የመዳን ተስፋ

ዘፍ 3፥15 ፣ ሉቃስ 1፥26-38

ሀ) እግዚአብሄር ያዘጋጀው የድነት መንገድ ምንድነው?

- ሰው ከአምላኩ መለየቱ መልካም ስላይደለ፤ በአንጻሩ ደግሞ እግዚአብሄር ጻድቅ ፈራጅ በመሆኑ ኃጢአት ሳይቀጣ መታለፍ ስለሌለበት፤ የሰው የኃጢአት እዳ የ ሚከፈልበትን የደኅንነት መንገድ እግዚአብሄር አዘጋጀ፡፡ ይህም፣ እውነትና መንገ ድ ሕይወትም በመሆን የጥልን ግድግዳ ያፈረሰው አስታራዊ ጌታችን ኢየሱስ ክ ርስቶስ ነው፡፡ (ዮሐ 3፤16፣ 2ቆሮ 5፤18.19፣ ዮሐ 14፤6)

- በአንድ ሰው (በአዳም) ምክንያት ሞት ለሰዎች ሁሉ እንደደረሰ፤ በአንዱ በክርስ ቶስ ኢየሱስ በኩል ደግሞ የዘላለም ሕይወት ለሰዎች ሁሉ ደረሰ፡፡ (ሮሜ 5፣ 15-21)

- ሰው የእግዚአብሄርን ትእዛዝ በመተላለፉ የተገፈፈው ጸጋ፣ የእግዚአብሔርን ቃል (ወንጌልን) በሚታዘዝበት ጊዜ ይመለስለታል፡፡ (ኤፌ 2፣ 5-9)

Can also be downloaded from:

http://www.j-e-c.org/faceliftup/Ministries/EvangelismMinistry/Salvation%20Teaching%20(Final_version).pdf

# 2. ድነት (Salvation)፤

## 2፣1 መዳን (Salvation) ምን ማለት ነው?

### 2.1.1 ትርጉሙ

«ድነት/መዳን ማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ከዘላለም ሞት ወደ ዘላለም ህይወት መሸጋገር ማለት ነው።»
(ዮሐ 11፡24-26) (ሮሜ 6፡22-23) (ዮሐ 3፡16፡ 36)
(ዮሐ 5፡24)

### 2.1.2 የደህንነት የእግዚአብሄር ጥሪ ነው።

*የደህንነት ጥሪ ማለት ሰው በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሄር የተለየ ስለ ሆነ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከራሱ ጋር እንዲታረቅ የፍቅር ግብዣ (ጥሪ) እግዚአብሄር ያደርግለታል። (ዘፍ 3፡9) (ቆላ 1፡20) (ምሳሌ 8፡1-5) (ሮሜ 5፡10) (2ቆሮ 5.18)*

*2.1.2.1 ከዚህ ዓለምና ከምኞቱ እንዲሁም ከሰይጣን ለመለየት ተጠርተናል*

**Sanctify**: (Greek hagiazo) set apart for sacred use or make holy (John 17:17)

መቀደስ የሚለው ቃል አንዱ ትርጉም «መለየት» ወይንም «መውጣት» ነው።

*2.1.2.1.1 ከምን ከምን እንድንለይ ተጠርተናል?*

1/ ከኃጢአት
«ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ...ራሳችንን እናንጻ።» 2ኛ ቆሮ 7፣1፤ ሮሜ 6፣20-23፤ 1ኛ ዮሐ 2፣1

2/ ከማያምነው አለምና ከዚህ አለም ሥርዓት፤

- «በማይመች አካሄድ ከማያምኑት ጋር አትጠመዱ» /2ኛ ቆሮ 6፤14-18/
- «ከመካከላቸው ወጡና የተለያችሁ ሁኑ፣ ርኩሱንም አትንኩ» መዝ 1፣1 ፤ ኢሳ 52፣11 ፤ 2ኛ ጢሞ 2፣22
- «አለምን ወይንም በአለም ያለውን አትውደዱ...» 1ኛ ዮሐ 2፣15-16
- ከዓለም የምንለየው ዓለም በክፉው /በሰይጣን/ ስለተያዘ ነው 1ኛ ዮሐ 5፣19

3/ ከጥንቆላና ከምዋርት፣ ከአስማት ወ.ዘ.ተ. እንዲሁም ከሰይጣንና የርሱ ከሆነው አስራር ሁሉ
ሐዋ 19፤13-20 ፣ ዘዳ 18፣9-14

*2.1.2.1.2 መለየት ስንል ምን ማለታችን ነው?*

1/ ይሄንን ስንል ግን ከአለም ወጥተን እራሳችንን አግልለን እንድንኖር አይደለም።
«ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንህም።» ዮሐ 17፣15

**Can also be downloaded from:**

*http://www.j-e-c.org/faceliftup/Ministries/EvangelismMinistry/Salvation%20Teaching%20(Final_version).pdf*

2/ በዓለም ውስጥ ሆነን ግን የአለም ብርሃንና
የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለሌሎች እንድናንጸባርቅ
ተጠርተናል፡፡ ፊል 2፣14-17

*2.1.2.2* *እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማገልገል ተጠርተናል*
ዘጸ 5፣1 ፤ ማር 3፣14-15

## 2.2 ከምንና እንዴት ነው የምንድነው?

### 2.2.1 ከምን?

1) ከሰይጣንና ከኃጢአት ባርነት (1ኛ ጴጥ 2፣9) (ቲቶ 3፣ 3-7)
(ሮሜ 8፣1-4) (ዕብ 2፣14-15) (ቆላ 1፣13)
2) ከዘለአለም ሞት፣ ከኩነኔ ፍርድ (ሮሜ 8፣1) ፤ (ሮሜ 8፣33)
3) ከገሃነም ፍርድ (ዮሐ 5፣ 24)

### 2.2.2 እንዴት? (ሰው ለመዳን ምን ማድረግ ያስፈልገዋል?)

*«ሰው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ኃጢአተኝነቱን አውቆ በእውነተኛ ን ስሃ ከክፉ መንገዱ በመመለስ ይድናል፡፡»*

ሉቃ 19፡6-10፣

1) ኃጢአተኝነትን አውቆ ንስዜ መግባት (ተዳጁቶ ከክፉ መንገድ መመለስ)
ሮሜ 3፣23 ፤ ሮሜ 3፣11-18 ፤ ሐዋ 2፣38 ፤ ሐዋ 3፣19-20
2) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ ሞታችንን እንደለወጠና በትንሣኤው ደግሞ ሕይወት እንደሰጠን ማመን
ሐዋ 16፣25-34 ፤ ሮሜ 4፣23-25 ፤ ሮሜ 6፣8-11
3) እግዚአብዉር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናችን የዘላለም ዊይወትን እንደሰጠንና ልጆቹም እንዳደረገን ማመን፡፡
ዮሐ 3፣16፤ ዮሐ 1፤12፣ ሮሜ 10፣9-10

Comment: በደንብ ጫን ተደርጎ እ ያንዳንዱን ጥቅስ እያነበቡ ጊዜ ወስዶ ማስተማር

## 2.3 ንስሃ

**ንስሃ ከእግዚአብሄር ጋር ያለንን ግንኙነት የምናድስበትና የምናስተካክልበት መንገድ ነው፡፡**

### 2.3.1 እውነተኛ ንስሃ ምንድነው?

1) በእግዚአብሄር ፊት ስለፈጸምነው ኃጢአት ከልብ መፀፀት
(መዝ 51፣ 1-4) (መዝ 38፣8)
2) ኃጢአትን ኃጢአት ነው ማለት
(ኃጢአትን አለመሸፈን) (መዝ 32፣5) (1ዮሐ 1፣9)
3) ከኃጢአት መመለስ (ኃጢአትን መተው)
ምሳሌ. 28÷13 ሆሴ 6፣ 1-2፣ ዕብ 12፣1
4) ኃጢአትን መጥላት፤
ሕዝ. 20÷43–44 ምሳ 8፣13
5) የንስሃ ፍሬን ማሳየት፣
ማቴ 3፣8 ፤ ሉቃ 19፣1-9 ፤ ዮሐ 8፣11

ቀደም ሲል በተደረገ በደል የተበላሸውን ነገር በማስተካከል ለአለም መልካም ምስክር መሆን

Can also be downloaded from:

http://www.j-e-c.org/faceliftup/Ministries/EvangelismMinistry/Salvation%20Teaching%20(Final_version).pdf

ዘሌ. 6፥1–7 ፤ ሉቃስ 19፥8

### 2.3.2 ንስሃ ምን ምንን ያካትታል?

1– ከክፉ ሥራና መንገድ መመለስ፤ ዘካ. 1፥4፤ ገላ. 5፥19–21፤ ኤፌ. 5፥5
2– ከዓለም መመለስ፤ 1ዮሐ. 2፥15–16 ፤ ያዕ. 4፥4
3– ከራስ መመለስ፤ 2ቆሮ. 5፥15 ፤ ሉቃስ 14፥26
4– ከሰይጣን መመለስ፤ ሐ.ሥራ. 26፥18 ፤ ቆላስ. 1፥13
5– ወደ እግዚአብሔር መመለስ፤ ዘካ. 1፥3 ፤ ኢሳ. 55፥6 ፤ ኢሳ. 31፥6
6– ወደ ትክክለኛ ኑሮ መመለስ፤ ሮሜ. 6፥13

### 2.3.3 በኃጢአት ወመቀስና መጸጸት ብቻ በራሱ ብቻ በቂ አይደለም፡፡፡

ሐ.ሥራ. 24፥25 2ቆሮ. 7፥10፤ ኢሳ. 64፥6 ማቴ.3፥7–10፤ ማቴ.5፥20 ያዕ. 2፥19–20 ፤ ሮሜ. 10፥10

## 2.4 መዳናችንን/ድነታችንን እንዴት እናውቃለን?

### 2.4.1 የድነት ማረጋገጫዎች

**ሀ – ሰው የዘላለም ህይወት እንዳለው ሊያውቅ ይችላል።**

1. እግዚአብሔር ሰው የዘላለም ሕይወት እንዳለው እንዲያውቅ ይፈልጋል። ሐዋርያው ዮሐንስ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ ይላል። 1ዮሐ. 5፥13

**ለ – የእግዚአብሔር ቃል ስለሚነግረው ሰው የዘላለም ሕይወት እንዳለው ሊያውቅ ይችላል። የሰው ስሜት ስለሚለውጥ ሰው በስሜቱ መታመን የለበትም። እግዚአብሔር ግን ግን አይዋሽም፤ ቃሉን አይለውጥም። ዕብ. 13፥8 ፤ማቴ. 24፥35**

1– ዮሐ. 3፥16 እና 36 በክርስቶስ ሁሉ የሚያምን የዘላለም ሕይወት እንዳለውና እንደማይጠፋ ይገልጻል።
2– ዮሐ. 3፥18 በክርስቶስ በሚያምን እንደማይፈረድበት ይገልጻል።
3– ዮሐ. 5፥24 በክርስቶስ የሚያምን ሁሉ የዘለለም ሕይወት እንዳለውና ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሸጋገረ ይገልጻል።
4– 1ዮሐ. 5፥12 ልጁ ያለው ሕይወት እንዳለው ይገልጻል።
5– ኢየሱስ እኔ የዘላለምን ሕይወት እሰጣችኋለሁ፤ ለዘላለም አይጠፋም፤ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም ይላል ዮሐ. 10፥28

**ሐ– ሰው የዘላለም ሕይወት እንዳለው መንፈስ ቅዱስ ይመሰክርለታል።**

1– መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ልጆች ይመራቸዋል። ሮሜ. 8፥14
2– መንፈስ ቅዱስ ለአማኙ የልጅነትን መንፈስ ይሰጠዋል። ሮሜ. 8፥15
3– መንፈስ ቅዱስ ከሰውየው መንፈስ ጋር ሆኖ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ይመሰክርለታል። ሮሜ. 8፥16
4– መንፈስ ቅዱስ አማኝ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሆን ያትመዋል። ኤፌ. 1፥13–14 ፤ 4፥30

Can also be downloaded from:

http://www.j-e-c.org/faceliftup/Ministries/EvangelismMinistry/Salvation%20Teaching%20(Final_version).pdf

### 2.4.2 አማኝ ደኅንነቱን እንዲጠራጠር የሚያደርጉ ነገሮች።

1ኛ አማኝ ኃጢአት ሲሰራ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ሕብረት ለጊዜው ይቋረጣል፤ ኃጢአት ስለ ሰራሁ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለሁም ብሎ ሊፈራ ይችላል። በኃጢአቱ ቢናዘዝና ቢተዋት ግን እግዚአብሔር ይቅር ይለዋል። 1ዮሐ. 1፥9 ፤ 2፥1 ፤ ምሳሌ. 28፥13

2ኛ ሰይጣን አማኙን ሊከሰውና ሊያጠራጥረው ይሞክራል። ራዕይ. 12፥10 ፤ ዘካ 3፥1

Comment: ተጨማሪ ጥቅሶችን ሙሴ ያመጣል

### 2.4.3 ስለ ደኅንነት ማረጋገጫዎች የተሳሳተ አመለካከት።

1ኛ የዘላለም ሕይወት አለኝ ስለዚህ ኃጢአት ብሰራ ምን አለበት? የሚል ሰው ተሳስቷል። ሮሜ. 6፥1–3 ፤ 15–19 ፤ 1ዮሐ። 5፥18

2ኛ እያንዳንዱ ሰው እውነተኛ እምነት እንዳለው ራሱን ይመርምር፤ 2ቆሮ. 13፥5 እውነተኛ አማኝ ኃጢአት ሲሰራ ስለ ኃጢአቱ ተጸጽቶ ይናዘዛል።

## <u>2.5 የመዳን ወጤት</u>

2.5.1 የእግዚአብሄር ልጅነት ሥልጣን ይሰጠዋል (ዮሐ 1፡12) (1 ዮሐ 3፡1)

- በጠላት ኃይል ላይ ድል ያገኛል (ሉቃ 10፡18-19)
- ወደ እግዚአብሄር ፊት የመቅረብ መብትና ድፍረት ኖረዋል (ሮሜ 8፡15)
- በኃጢአት ልምምድ ያለመቀጠል (ሮሜ 6፡6፤ 1ኛ ዮሐ 3፡9 ፤ 5፡18)

2.5.2 ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ይሸጋገራል፡፡ (1 ጴጥ 2፡9) (ቆላ 1፡13-14)

2.5.3 አዲስ ፍጥረት ይሆናል (2 ቆሮ 5፡17)
2.5.4 የእግዚአብርን ምህረት ያገኛል (1 ጴጥ 2፡10)
2.5.5 የጽድቅን ስጦታ ያገኛል (ኤፌ 2፡8-9)

## <u>2.6 የመዳን ሂደቶች(Justification, Sanctification and Holiness)</u>

### ሀ) መጽደቅ (Justification)

- ጽድቅ ስጦታ ነው፡፡ 2.5.5 ን ይመልከቱ፡፡
- ለድነት የሚያበቃው ጽድቅ በእኛ መልካም ሥራ የሚገኝ ሳይሆን ከእግዚአብ ሔር ዘንድ በስጦታነው የሚገኝ ነው፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመናችን ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርልናል፡፡

**ሮሜ 4፡24-25 ሮሜ 3፡20-26 ፤ ሮሜ 4፡15 ፤ 1ኛ ቆሮ 6፡11 ፤ 1ኛ ቆሮ 1፡30**

### ለ/ መቀደስ (Sanctification) (ክርስቶስን እየመሰሉ ማደግ)

**አንድ አማኝ ክርስቶስን ከተቀበለ ጊዜ ጀምሮ በሕይወቱ ባለማቋረጥ የሚካሄድ ራስን ለእግዚአብሔር የመለየት <u>ሂደት</u> መኖር ግዴታ አለበት።**

**Can also be downloaded from:**

*http://www.j-e-c.org/faceliftup/Ministries/EvangelismMinistry/Salvation%20Teaching%20(Final_version).pdf*

ሮሜ. 6፥22 ፤ 2ቆሮ. 6፥17
**ቅድስናን በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚያካሂደው እግዚአብሔር ሲሆን አማኙ ደግሞ እራሱን ለእግዚአብሔር በማቅረብ እግዚአብሔር በውስጡቅድስናን እንዲፈጽም መታዘዝ አለበት።** 2ቆሮ. 7፥1 ፤
1ተሰ. 5፥23–24 ፤ **ፊልጵ.** 2፥12

**«እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» (1ኛ ጴጥ 1፣15-16)**
**«እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እናንተም እኔን ምሰሉ» (1ኛ ቆሮ 11፣1)**
**እግዚአብሔር ወደራሱ የቅድስና ደረጃ እንድንጠጋ ይጋብዘናል፡፡ እግዚአብሔር በዚህ ምድርላይ ያለማቋረጥ ወደቅድስና ሕይወት፣ እርሱን ወደመምሰል እንድንጠጋና ከክብር ወደክብር እንድንለወጥ ይወዳል፡፡ 2ኛ ጴጥ 1፣2-3፤**
**1ኛ ጴጥ 5፣10፤ 2ኛ ቆሮ 3፣18**

### ሐ/ ምልዓተ ቅድስና (Holiness)

**በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው የክርስቶስን መገለጥ ለሚጠባበቁ በመጨረሻው ዘመን የሚገለጥ የመዳን ፍጻሜ ነው።**
**ዕብ.** 12፥23 ፤ **ፊልጵ.** 3፥20 ፤ 1**ቆሮ.** 15፥43–49
**ክርስቶስ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ አሮጌው ሥጋችን በአዲሱ አካል በሚለወጥበት ጊዜ ቅድስናችን ፍጹም ይሆናል።**

## <u>2.7 የኢየሱስ ክርስቶስ ደም</u>

1– **ደሙ ኃጢአትን ያስተሰርያል፤** ዕብ. 9፥14–22 ፤ ኤፌ **1፣7**
2– **ደሙ ከኃጢአት ያነፃናል። 1ኛ**ዮሐ.1፥7፤ ዕብ. 9፥14
3– **መልሶ ይገዛናል (ይዋጀናል)**
<u>መዋጀት/መቤዠት ማለት፤</u> ***በሌላ ዘንድ የሚገኝን የራስን ንብረት ዋጋ ከፍሎ ማስመለስ ማለት ነው፡፡***
ኤፌ. 1፥7 ፤ 1ቆሮ. 6፥20 ፤ ሐ.ሥራ. 20፥28 ፤ 1ጴጥ. 1፥18–19
4– **ከኃጢአት ክስ ያድነናል፤** ዕብ. 9፥14 ፤ ራዕይ. 12፥10–11
5– **ይቀድሰናል፤** ዕብ. 13፥12 ፤ ቆላስ. 1፥20–22
6– **ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቀናል፤ (ወደ እግዚአብሔር ያቀርበናል)**
ቆላስ. 1፥20–22፤ ኤፌ **2፣13**
7– **ወደ እግዚአብሔር ሕልውና እንድንገባ ድፍረትን ይሰጠናል፤**
ዕብ. 10፥19–22

## <u>2.8 ፀጋ</u>

### 2.8.1 የፀጋ ትርጉም

ሀ– ለማይገባቸው ሰዎች የሚሰጥ የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ነው።
**1ኛ ቆሮ 15፣9-10** ፤ ኤፌ. 2፥8–9
ለ– በጽድቅና እግዚአብሔርን በመፍራት እንድንኖር የሚያስችል የእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡
**ቲቶ 2፣11-13**

### 2.8.2 መዳን በፀጋ ነው

*ድነት የሚገኘው በጸጋ ነው። ጸጋ እግዚአብሔር ዋጋ ከፍሎበት ለእኛ በነጻ የሰጠን የምሕረቱ ውጤት ነው። ጸጋ ነጻ ስጦታ ስንል እኛ ዋጋ አልከፈልንበትም ማለታችን ነው እንጂ ዋጋ አልተከፈለበትም ለማለት አይደለም።ድህንነትን ለእኛ ነጻ ለማድረግ ክርስቶስ የራሱን ሕይወት ሰጥቶናልና። ስለዚህ ሰው ለደህንነቱ ይህን ጸጋ ከመቀበል በስተቀር የሚያደርገው ምንም ነገር የለም። የእግዚአብሔርን ጸጋ*

*ለመቀበል እምነት አስፈላጊ ነው። የዚህ ጸጋ መቀበያ እጅ እምነታችን ነው። ያ ለ እምነት መዳንም ሆነ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም።*
**ኤፌ.** 2፥5–9፤ **ሐዋ 15፣11፤ 2ኛ ጢሞ 1፣9 ፤ ዕብ 11፣6**

### 2.8.3 የፀጋ ሥራ (ሚና)

1– ድነትን ያስገኝልናል፤ ቲቶ. 2፥11–13
2– በሚያስፈልገን ጊዜ የሚረዳንን ኃይል ሰጪ ነው፤ ዕብ. 4፥16
3– የቅድስናን ኑሮ መኖርን ያስተምረናል/ ያስችለናል፤
ቲቶ.2፥11–13
4– **መከራን መቋቋምና በድል ማለፍ ያስችለናል**
**2ኛ ቆሮ 12፣9 ፤ ሮሜ 5፣1 ፤ ፊል 1፣28-29 ፤ 1ኛ ጴጥ 5፣10 ፤**
**1ኛ ቆሮ 15፣9-10 ፤** ያዕ. 4፥6 ፤ 2ቆሮ. 12፥9 ፤

## <u>2.9 እምነትና ሥራ</u>

**«እምነት ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደሚፈጸም እርግጠኛ የምንሆንበት፣ የማናየውም ነገር እውን መሆኑን የምንረዳበት ነው።» ዕብ 11፣1**

**??? ሥራ በተግባርና በሃሳብ የምናከናውነው ድርጊት ነው። ???**

**2.9.1 መዳን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ የሚገኝ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ነው።**
**ሮሜ.** 3፥27–28 ፤ 4፥4–8 ፤ 9፥31–33 ፤ 10፥3–4 ፤ **ኤፌ.** 2፥8–9

2.9.2 **እምነት ያለ ሥራ ሙት ነው።**
**ያዕ.** 2፥14–26

**እምነትን በሥራ መግለጽ**

– እምነት ያለ ሥራ ሙት ነው ስንል ሰው እምነቱን (የሕይወት ለውጡን) በተግባር መግለስ አለበት ማለታችን ነው፤
**ፊልጵ.** 2፥12–13 ፤ **ማቴ.** 7፥21–27
– ቢሆንም የጽድቅን ሥራ የምንሰራው ለመጽደቅ ወይም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ሳይሆን ስለ ጻደቅን የምንፈጽመውን መልካም ሥራ ማለታችን ነው።
**ሮሜ 10፣3-4፤ 1ኛ ቆሮ 1፣30 ፤ ሮሜ 3፣19-20፤ ራእ 19፣7-8**

# <u>3. ኪዳን (እግዚአብሄር ከሰው ልጆች ጋር የገባው ቃል ኪዳን)</u>

## 3.1 ኪዳን ማለት ምን ማለት ነው?

- **ውል ወይንም ስምምነት ማለት ነው። ()**

**<u>ዘፍ</u>** <u>9.16</u> *ቀስቱ በደመና ላይ ተገልጦ በማይበት ጊዜ ሁሉ፣ በእኔና በምድር ላይ ባሉ ሕያዋን ፍጡራን መካከል ያለውን ዘላለማዊ ኪዳን አስባለሁ፡፡*

**<u>ዘፍ</u>** <u>26.28</u> *እነርሱም እንዲህ አሉ፤ ኗ እግዚአብሔር -ያህዌ ? ከአንተ ጋር መሆኑን በግልጽ ተረድ ተናል፤ ስለዚህም፣ ዩበመሐላ የጸናውል በመ ካከላችን መኖር አለበት ጸ አልን፤ ይህም በእ ኛና በአንተ መካካል የሚጸና ውል ነው፤ አሁንም ከአንተ ጋር ስምምነት እናድርግ፤ 29 አንተን እንዳልጠጐዳንህ፣ ነገር ግን በጎነ ትን እንዳሳየንህና በሰላም እንደ ሸኘንህ ሁሉ፣ አንተም ክፉ እንዳታደርግብን በመ ካከላችን ውል ይደረግ፤ አንተን እንደሆን መቼም እግዚአብሔር -ያህዌ ? ባርኮሃል፡፡ ቃ*

## 3.2 ሁለቱ ኪዳኖች (ብሉይና አዲስ)

**Can also be downloaded from:**

***<u>http://www.j-e-c.org/faceliftup/Ministries/EvangelismMinistry/Salvation%20Teaching%20(Final_version).pdf</u>***

### 3.2.1 ብሉይ (ፊተኛው/የቀደመው) ኪዳን፤

- ✓ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ከተለያዩ ሰዎች ጋር ኪዳን (**ስምምነት**) አድርጓል።
- ✓ ዋናው ኪዳን ግን በሙሴ አማካኝነት ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን ነው።ዘጸ. 19፥1–8
- ✓ ይህም ኪዳን የሕጉን ትዕዛዛት በመጠበቅ ላይ የተመሰረተ ነበር። ያዕ. 2፥10፥ ሮሜ 2፥13፥ ገላ 5፡2-3

### 3.2.2 አዲስ ኪዳን

እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ዓለምን ከራሱ ጋር ያስታረቀበት አዲስ መንገድ ነው። 2ኛ ቆሮ 5፡18-19፣ ሮሜ 5፡10፣

ይኸውም ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገለትን የመስቀል ሥራ በእምነት በመቀበል የሚሆን መዳን ነው። ዕብ. 9፥15–22 ፥

## 3.3 በሙሴ አማካኝነት የተሰጠው ሕግ

### 3.3.1 የሕግ ሚናና አገልግሎት (የተሰጠበት ዓላማ)

ሀ/ ሰው ቢያደርገው ኖሮ በሕይወት የሚኖርበት ሕግ ተሰጥቶት ነበረ፡፡ (ሕዝ 20፡10-11 ና 13)
ሆኖም የሰው ልጅ በኃጢአተኛ ባሕርዩ የተነሳ የተሰጠውን ሕግ ሊጠብቅ አልቻለም፡፡
(ሮሜ 8፡3)

ለ/ ኃጢአት ምን እንደሆነ ለማሳወቅ፤
(ይህም ማለት ኃጢአት የሆነውንና ኃጢአት ያልሆነውን ለመለየት ነው።)
ሮሜ. 3፥19–20 ፤ ሮሜ. 7፥7፤ 1ኛ ጢሞ 1፡8-11

ሐ/ የሰውን ዘር ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚት ነው፤
ዕብ. 10፥1 ፤ ገላትያ 3፥21–24

መ/ ሰው በራሱ ሥራ መጽደቅ እንደማይችል ለማሳወቅ፤
ሮሜ. 10፥3

### 3.3.2 ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነው፤ ማቴ. 5፥17–18 ፥ ሮሜ. 10፥3-4 ፥ ገላ 4፣ 4 -5

ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነው ስንል ለሕጉ ፍጹም በመታዘዝና የትንቢት ቃሎችንም ተግባራዊ በማድረግ ሕጉን ሙሉ ለሙሉ ፈጽሞታል ማለት ነው።

### 3.3.3 ሰው ሕግን በመጠበቅ ይጸድቃልን?

ሮሜ. 3፥11–28 ፣ ሮሜ 4፣5 ፣ ዕብ 7፣18-19፣ ገላ 5፣4

## 3.4 በእምነት የሚገኘው መዳን - የእምነት ሕግ

- ወደ አብ መቅረቢያ አዲስ መንገድ
  ሮሜ 3፣20-28፣ ሮሜ 5፣1-2 ፣ ዕብ 10፣15-23 ፣ 1ኛ ጴጥ 1፣5

Can also be downloaded from:

http://www.j-e-c.org/faceliftup/Ministries/EvangelismMinistry/Salvation%20Teaching%20(Final_version).pdf